# ክልል የመለስ  አገር አፍራሽ መርገም ት ፤ *የችግሮቹ ሰንኮፍና በዲሞክራሲ መፍትሔዎች*

ክልል የህዝብ ችግሮች ሰንኮፍ፣ ማለት የጥፋቶች መሰረት ስለሆነ ይደምሰስ ፣ ይጥፋ ፣ ይህ ብቻ ቢሆን ነው ከክልል ጋር የመጡት ሀገራዊ ጣጣና ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት። ክልል ተደምስሶ በምትኩ ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስትና ስርአቶች በአገራዊ ፣ በየክፍለሀገራት ፣ በአውራጃዎችና በወረዳዎች ተመስርተው ህዝባዊ አስተዳደር ሰላም አንድነትና እድገት ሊኖር የሚችለው ። ስለዚ የሚከተሉት አገር አቀፍ ችግሮች ከክልል ጋር ይደምሰሱ ። መደምሰስም አለባቸው አስር የክልል ምክንያት ከተፈጠሩት ችግሮች ዋና ዋና የሆኑትን እንገንዘብ ።

| **ችግሮች** | **ምክንያት** | **መፍትሄ** |
|---|---|---|
| **ዘረኝነት** | ክልል | ዲሞክራሲ፣ ከመ ሀሪ አገር ቶስከ ወረዳ |
| **መገዳደል** | ›› | ›› |
| ጥላቻ | ›› | ›› |
| መከፋፈል | ›› | ›› |
| ስደት | ›› | ›› |
| ሽብር | ›› | ›› |
| ዝርፍያ | ›› | ›› |
| መፈናቀል | ›› | ›› |
| ስራ እጦት | ›› | ›› |
| አገር መቆራረስ | ›› | ›› |
| **ሌሎችም፣ሌሎችም** | ›› | ›› |

## *እንግዲህ  የክልል ድቀት ፣ መዘዝና ሰቆቃ እነዚህና የመሳሰሉት ናቸው ።*

በአካባቢዬ  ካላት አንድ ካህን ጋር ስለ ክልል ስንወያይ እንዲህ አሉ ። **ክልል ማለት መጋረጃ ፣ ሽፋን ፣ ላለመታየት መከለል ማለት ነው** ሲሉ የማውቀውን ነገሩኝ። እንዲሁም አንድ ሌላ ሰው ሲናገሩ **ክልል ማለት ድንበር** ፣ ወይም **ወስን መካለል ማለት ነው** ። ከዚህ **አትለፍበኝ** ፣ **አልደርስብህም በመባባል ተለያይቶ ለመኖር የሚያስችል ውሳኔ ነው** ሲሉ ደመደሙልኝ፡ ፡`

ይህን ከመሳሰሉት በመነሳት ፣ **ክልል ማለት አንዱ ከሌላው ተለያይቶ መኖር ያለበት፣ መገናኘትም የሌለበት** ማለት ሲሆን ፤ በሌላው ዳግም **አንዱ የሌላውን ድንበር ማለፍ የሌለበት ነው። ያለበለዚያ ግን ፀበኝነት ፤ መጠላላት ፤ መወነጃጀል ፤ ከባሰም በጦርነት መጠፋፋት ይሆናል ማለት ነው።**

ይህ ሁኔታ በማያከራክር መልኩ ለተማረና ለአወቀው በትክክል **የቅኝ ግዛት ስርአት** ነው ። (characteristics of colonial systemን google አድርጎ ማየት ነው) ። ይህ **ለያይተህ አዳንቁረህ ግዛው የሚለው የቀኝ ግዛት ገፀባህሪ በኢትዮጵያ ላይ በትክክል መተግበሩ ግልፅ ነው ።**

የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ እንደተባለው ይህ የቅኝ ግዛት እና የመጣው **የክልል በሽታ በኢትዮጵያ ላይ የተጣለው ከኢትዮጵያ ከአብራኳ በተፈጠሩት፣ የጠቡትን ጡት ነካሽ እና የበሉበትን ገል ሰባሪዎች በመሆን አዙረውም ማየት ያልቻሉ ጥቂቶች ልጆቿ መሆኑ ግልፅ ነው** ።

## የክልል የችግሮች መዘዝና ህዝባዊ ጉዳዮች

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ላይ የሚደርሱትን የክልል መዘዞች ፣ ቤቶችና መንደሮች ፣ ወንዞችና ተራሮች ይቁጠራቸው።

ለምሳሌ ያህልም ለመጥቀስ የሚከተሉትን እንገንዘብ ፤

1. *በየዘር ጥላቻዎች ፣ ለስደት ፣ ለመፈናቀል (ለምሳሌ በቤኒሻንጉልና በደቡብ) ለመገዳደል፣ ለመጠፋፋትና ለጦርነትም (ለምሳሌ ያህል የሶማሌው ሁኔታ) ፣በክልል ምክንያት ተባዛ።*
2. *የዘር ፖለቲካ ያመጣው የድንበርና የወሰን ግጭቶች ፣በክልል ምክንያት ችግሮችን ያመጣ።*
3. *በህገመንግስት ተብዬውና ለአንድ ጎሳ ጥቅም የተነደፈውና የተፃፈው አንቀፅ 39 መሰረት አገር ለመገነጣጠል የሚደረገው የአክራሪነቶች ከበሮ ድለቃ ፣ህዝቡን አደናቆረው።*
4. *የሰላምና የአንድነት፣ የዜጋነትም ምልክት የሆነውን የኢትዮጵያን ነባር ሰንደቅ ዓላማ በሌሎች አልነበሬ ምልክቶች ለመተካትም ሆነ ለማጥፋት የክልሎች ሸብረብ ተባዛ።*
5. *በአንድ አገር ውስጥ ክልል በማብዛት የፕሬዝዳንቶች ብዛትና ጋጋታዎች በክልሎች ነገሱ።*
6. *በሀይማኖት ላይ ተፅእኖ በማድረግና መሪዎችን በመከፋፈል ብሎም በማሰር ፣ በመደብደብ ፣ መግደልም ተጨምሮ በክልሎች ስቃይና መከራዎችም ተበራከቱ።*
7. *በተለይም ሁለቱን ታላላቅ ብሔረ ኢትዮጵያዊያንን፤ ማለትም አማራንና ኦሮሞን፤ ማጣላት ፣ ከዚያም በክልል አማካኝነት አማሮችን ከቤኒሻንጉል ፣ ከደቡብና ከምስራቅ እየተደበደቡ እንዲፈናቀሉና ይባስም ብሎ እየተገዳደሉ ፣ ለአራዊት መገቢቻው ፣ የቀሩትም በነፍስ አውጭኝ ተሰደዱ ፣ መድረሻም ሆነ ተቀባይ እስከማጣት ደረሱ በክልል ምክንያት።*
8. *ለአንድ ጎሳ ጥቅምና አገዛዝ ይሆን ዘንድ የመሬት ቆዳ ስፍራት መሠረት የነበሩት የክፍለሀገሮች ተቆራረሱ። ለምሳሌ (1) ራያ ፣(2) አፋር (3) ወልቃይትና ጠገዴ ሌሎችም እንዲሁም በመሆን ሰላም እጦትና በአምባገነኖች ጦርነቶች ህዝቦቹ ይታመሳሉ ፣ ይገዳደላሉ ፣ ይፈናቀላሉ ፣ ይበዳደላሉ ።*
9. *በታወቁም ሆነ በተሸፋፈኑ ምክንያቶች ብዙ አካባቢዎችን (ለምሳሌ ደንቢ ዶሎ) አምቆ እድገት በመከልከል ህዝቡን ለእልቂትና ለመከራ ዳረጉ። ደንቢ ዶሎም አለቀላት ተስፋ አይኖራትም የተባለችውን በአንድ ሰው (በዶ/ር አበራ መሸሻ) ጣልቃ ገብነትና መስዋትነት ዛሬ የከተማዋ አካባቢዎች በአራት አመታት ውስጥ ታላቅ ለውጥና እድገት ተጎናፅፈዋል። ሆኖም ግን ዛሬም በክልል ምክንያቶች በዚያ አካባቢ የሚሰማው ያሳዝናል።*
10. *እነዚህና የመሳሰሉ ሌሎችም የመከፋፈያ ስልትና አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝባዊ ታሪክና ልማድ ማኮላሸት የሚጠቀሱ ናቸው፤ በክልል ምክንያት።*

እነዚህን በግልጽ የቅኝ ግዛት ስርዓቶች በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ተጭነው ለሀያ ሰባት አመታት አገሪቱን በመገነጣጠል ላይ የተሰማሩ። ይሁን እንጂ ህዝቡ በመንፈስ ጠንካራነት በህብረተሰባዊትና በአንድነት ሰንሰለት የክልልን ሰቆቃ በልማዳዊ እንቢተኝነት ተቋቋመው።

ስለሆነም እነሆ ለብዙ ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የቅኝ ግዛት ሐይል ያስመጣቸው ቅን አገልጋዮች አገሪቱን በዘረኝነት ክልለው ሰላምና የአንድነት ጠፉ። በአገሩቱም ላይ ውድቀትና ድቀት እየተስፋፋ ያለበት ላይ ደርሳለች ።

ብዙ ተነግሯል ብዙ ተብሏል ብዙ ፍጅትም ተካሂዷል። ሁሉንም ወይም በጥቂቱም ቢሆን በመፅሀፍ ደረጃ ካልሆነ በዝህች አይነት አጭር ፅሁፍ ማብራራት አይቻልም። ሆኖም ግን በአጭሩ ለማለት ያህል **<u>ክልል</u>** የችግሮች መንስኤና **<u>ሰንኮፍ</u>** ስለሆነ ሰንኮፉ ካልወጣ የእባጭ በሽታ እንደማይድን ሁሉ ክልልም ካልተደመሰሰ ኢትዮጵያ ቀድሞ ወደነበራት ሰላምና አንድነት መመለስ በምንም አይነት አትችልም። ለሁሉም ችግሮች መሰረታዊና በዋናነትም መነሳት ያለበት ሲያስቡትም የሚገለማ ክልል የሚባል የፖለቲካ መዋቅር ነው። ክልል የእባጭ አይነት የሰንኮፍም ህመም ነው።

እባጭ የሚባለው መጥፎ በሽታ ታመው የደረሰላቸው ባይታመሙትም በሌሎች ላይ አይተውት የተገነዘቡ በብዛት ይኖራሉ። እንግዲህ የእባጭ ሰንኮፋ ካልወጣ ሰው ከዚያ መጥፎ በሽታ ሊድን አይችልም ።

***<u>አቤት የእባጭ ቁስል የህመሙ ጣጣ</u>***

***መዳንም አይቻል ሰንኮፉ ካልወጣ***

# የክልል ጣረሞት

ለክልል መወገድ ሀሳቦች እየፈለቁ ነው። ለምሳሌም የሚከተሉትን መጥቀስ ያስፈልግ ይሆናል።

***1. ልዑልና ሀያሉ እግዚያብሄር ይባርካቸውና ፤***

***ሀ) ፕሬዝዳንት ለማ መገርሳ በባህርዳር ከአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር ሆነው የኢትዮጵያዊነት ሱስና አንድነት አውጃው ታዳሚውን ሕዝብ በደስታ እያስለቀሱ ያስጨፈሩ ዕለት ክልል ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ታወጀ፣ ክልልም ታመመች ።***

***ለ) ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ "ኢትዮጵያዊያን ስንኖር ኢትዮጵያዊያን ስንሞት ኢትዮጵያ ነን" ብለው በፓርላማ ውስጥ ያወጁ ዕለት በኢትዮጵያውያን ልቦናዎች ውስጥ ክልል ጣረሞት ውስጥ ገባች ።***

***2. በክልል እየተሰየሙ የመለስ ዕራእይ (ለኢትዮጵያ ማጥፋት) ፕሬዝዳንት ተብዬዎች የህዝቡ ፀረሰላም የሆኑ (ለራሳቸው ህዝቦች ፀር የሆኑ እንደነ አብዲ ኢሌ የሱማሌ ክልል ሽፍታ) ሲወገዱ ጥሪው ክልልን ማጥፋት እንደሚሆን አያጠራጥርም ።***

***3. አርቲስት ታማኝ በየነ፤ እንደ ብዙዎች ሀቀኞች ኢትዮጵያውያን ፤ በቅርቡ ኢትዮጵያን ሲጎበኝ "ክልል ይወገድ" ሲል ተሰማምቷል።***

***4. ጳጉሜ 4 ቀን 2010 ዓም በዋሽንግተን ዲሲ በመድሀኒያለም ቤተ ክርስትያን ምዕመናን ተሰብስበው ለሚመጣው አዲስ አመት ክልል ይጥፋ እያሉ ጮኋል። ይኸውም በመላው ኢትዮጵያዊያን እና በባለስልጣኖች ልቦናዎች ውስጥ የክልል መጥፋት ግልፅ የሆነ ነው፤ ከጅቦቹ በስተቀር ፤ ሌሎችም በብዛት ሊጠቀሱ ይችላሉ።***

# <u>የሕገመንግስት</u> መለወጥ <u>ለቋሚ</u> ሥርአተ መንግሥት

በክልል ምክንያት መበታተንና መቀናነስም ስለበዛ በወቅቱ የመደመር መርሆ እየተስተናገደ ነው። ሰላምና ፍቅርም እንዲሁ በክልል ምክንያት እየጠፋ ስለሆነ በሰላምና በፍቅር ሕዝቦች አንድ እንዲሆኑ የሚለውን ጥሪ እየተስተጋባ ነው።

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቋቋም ክልልን ለአንዴና ለምንግዜም ማስወገዱ አስፈላጊና አንገብጋቢ ሲሆን መፍትሄውም አንድና አንድ ብቻ ነው ። ይሀውም የሕገመንግስቱ መለወጥ ነው ።

ሕገመንግስት በዳር ድንበር ተወስኖ ለሚኖር ህብረተሰብ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ስርአተ መንግስት ነው። በባለሙያዎቹ ማለት እውቀትና ችሎታ ባላቸው ሰዎች ተዘጋጅቶ አስተዳዳሪዎችና ተዳዳሪዎች መሪዎችና ተመሪዎች በጋሪዮሽ ተስማምተው የሚቀበሉት የህብረተሰብ መተዳደሪያ ደንብ ነው። መንግስት ማለት ህዝብ ማለት ሲሆን ሕገመንግስት ማለት ዳግም ህዝባዊ መተዳደሪያ ስርአት ደንብ ማለት ነው ።

ህገመንግስት በነገስታት (እንደ ዘውዳዊ ዘመን) በወታደራዊ (እንደ ደርግ) ወይም በአንድ ፓርቲና ዘረኝነት (እንደ ህወሐት) ፀረህዝብ የሆነ አምባገነናዊ ስርአት አይደለም፤ መሆንም የለበትም። እንደሚታወቀውም የአምባገነኖች ስርሀት ከመሃል አገር (ከአዲስ አበባ) ወደ ክፍለሀገሮች ፣ ወደ አውራጃዎችና ወረዳዎች ሹመት ወደታች እየተሰጠ ተሿሚዎች በቀደምለት ጃንሆይን ትላንት መንግስቱ ኃ/ማርያም በቅርቡ መለሰንና አሁንም በመቀጠል የመሀል አገርን ስልጣን የሚፈራም ማምለክ እንጂ ህዝብን የሚያከብር እና የሚራራም አይደለም። በተቃራኒው፣ ህዝባዊ ሥርአተ መንግሥት ከላይ እስከ ወረዳ ከዚያም አስከ ቀበሌ ባለስልጣናት በቀጥታ በህዝብ መሾምና መሻርን የሚያስተናግድ መሆን ይኖርበታል።

የዚህ አይነት ስርአተ መንግስት በምንም መልኩ በአንድ አላማ ፓርቲ (ሰይጣናዊ ሄዶ መላካዊ ቢመጣ) የሚያስተባብር ሊሆን አይችልም። የሚወተበትም ዲሞክራሲያዊ (grassroots- የስርዶ - democracy) ፋይዳ ቢስ ጮሀት እንጂ ህዝባዊ ጥቅም አይኖረውም ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው ጣጣ የፓርቲ ብዛት ጋጋታ ነው። ሁሉም ለአዲስ አበባ የአምባገነንነት ስልጣን ሽሚያ እንጂ ለህዝብ አገልግሎት አይመስልም። ስለዚህ ለህዝብ ከታሰበ ዲሞክራሲ እያለ የሚጮህው ሁሉ በአንድ ላይ ሆኖ እንበል **<u>አገራዊ ወይም ህብረተሰባዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲ</u>** (**National or Social Democratic Party**) ይመስርት። በዘር ፣ በምድር ፣ በሰማይ ፣ በወንዝ ፣ በተራራምና በሌሎች ትርጉመቢስ ፓርቲዎች ስም ለህዝብ አይደናቆር ፤ አይበጅምና ፤ አንድነትንና ሰላምንም ሊያመጡ አይችሉም።

የኢህዲግ ፓርቲ የጎዳና አሮጌ ቤቱን እያደሰ ይበቃናል ንፁህ ነን ኑ ግቡ እያለ ነው። መልካም ነው ይቀጥል ፣ ግን አንድ አገር አቀፍ የሆነ "ብዴፓ" በሰፊው ተቋቁሞ ለህዝብ የሚሆን መልኩ ከማህከል እስከ ወረዳ ለሁሉም ህዝቦች ተዘርግቶ ለመስራት ከኢህዲግ ጋር በወዳደር ሰላምና አንድነትን ሊያመጣ ይችላል። ይኸውም በአስቸካይ ሥርአተ መንግሥት ተዘጋጅቶ አገራዊ ሰላምና በአንድ ሰንደቃላማ ስር ህብረት ሊመሰረት ይችላል። በየክፍለ አገሮች፤ አውራጃዎችና ወረዳዎች ሥርአት መንግሥት ተዘርግቶ የአንድ ፓርቲ አገልግሎት በአማራጭነት ለህዝብ ቢቀርብ ለኢህዲግ እርዳታ ነው ።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ ጥቅምት 21/2011 በአውሮፓ ለተቀበሏቸው ለኢትዮጵያን ሊመለሱ የኢህዴግ ክልልን እንጂ ለክፍለሀገር በግዜው ትኩረት እንደማይሰጠው አብስረዋል ። ሌሎችም የኢህዲግ ባለስልጣናት እንዲሁ እንደሚያስቡ አያጠራጥርም የፓርቲያቸው ፤ ሀላፊነት አለባቸውና ።

ስለዚህ **<u>አገራዊ ወይም ህብረተሰባዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲ</u>** ህዝቡን ለማነሳሳትና ከኤህዴግ ጋር ተወዳድሮ ለማሸነፍ የሚከተሉት አይነት የፓርቲ ፕሮግራሞች በማንሳት ክልልን መደምሰስ ይቻላል ።

1. ***የክፍለሀገር ችግሮችን እያወጁ ክልልን ማውገዝ ፤***
2. ***በክልል ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ የደረሱትን አበሳዎች እያብራሩ ክልል እንዲወገድ ማድረግ ፤***
3. ***ዲሞክራሲን ከመሀል ሀገር እስከ አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲተገበር ለህዝብ ማወጅ፤***
4. ***የመለስን አገር አፍራሽና ፀረህዝብ እርኩስ ራዕይ በመቃዎም ኢህዴግን መሮካከር ፤***
5. ***ሌሎችም ህዝባዊ ጥቅሞችን እያወጁ ለሚመሰረተው ፓርቲ ተቀባይነት ማስገኘት ፤***
6. ***ይህንን ለማድረግ ግዜው አሁን ስለሆነ ይህንን የሚያስተባብር ተቋምና ሂደት መፍጠር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ፤***
7. ***ሌሎችም ፤ ሌሎችም።***

**ከዶ/ር አበራ መሸሻ** ፤
የህዝባዊ አስተዳደር ፕሮፌሰር ፤ NSU
የቀድሞ የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባኤ ሊቀመንበር

*Sincere gratitude to Ms. Nebiat B. Melese*
*of Kia Travel Agency, in D. C.*
*for assisting in typing the document*

===================================================================================

**REQUEST,** To have better understanding of the writers call for Constitutional Democracy, in regard to the above given ideas, all concerned are requested to have copy of a book: ***<u>Constitutional Democracy for Public 'Self' Administration</u>***, *<u>Legislative Empowerments at National, Regional, Districts and Local governances,</u>* for $39.95 (and $3.55 for shipping and handling). The book is available through an email address: **ameshesha18@gmail.com.**